ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)
Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)
Website: www.moreshwegenie.org E-mail: InfoAndPR@moreshwegenie.org
ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት | እሮብ፣ ጥቅምት 24፣ ፪ሺ ፲፫ ዓ.ም. (Oct 4, 2020) | ቅጽ ፯ ቁጥር ፳፪

# በግፍና በመድልዎ የታጨቀው የኢህአዴግ/ብልፅግና አገዛዝ ስልጣኑን ለኢትዮጵያ ህዝብ አስረክቦ ይልቀቅ!

ፀረ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አቋም ያለው የቀድሞው ኢህዴግ የአሁኑ ብልፅግና ስልጣኑን በድጋሚ ለመያዝ ሲል፤ እኛ ኢህአዴጎች አሸባሪዎች ነበርን፤ የተቃወሙንን አሸባሪ ስንል፣ ስናሳድድ፣ ስናስር፣ አስረን ብልት ስናኮላሽ፣ ጥፍር ስንነቅል፣ ወ ዘ ተ ነበር፤ ይቅር ባዩ የኢትዮጵያ ህዝብ ይቅርታ ያድርግልን፤ ብለው ተማፅነው፣ የኢትዮጵያን አንድነትና ሰላም አስጠብቄ እኔ አሻግራችኋለሁ ብለው ቃል የገቡት በዶ/ር አብይ አህመድ የሚመራው ኦዴፓ/ብልፅግና ስልጣን ከያዘ በኋላ አገሪቱ በአሳዛኝ ሁኔታ ከመቸውም በበለጠ በከፍተኛ አለመረጋጋትና ቀውስ ውስጥ ትገኛለች ። ጠቅላዩ እንደጉም በኖ በጠፋ የተስፋ ቃላቸው ታምኖ በደስታና በእልልታ የተቀበላቸውን ህዝብ "ከህይወት ወደሞት" በማሸጋገር ላይ መሆናቸውን አጥብቀን እናወግዛለን።

የሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት በአገዛዙ እውቅናና ቸልተኝነት በተደጋጋሚ በነገዳቸው አማራ፣ በሀይማኖታቸው ኦርቶዶክስ ተዋህዶ፣ በስነልቦናቸው የኢትዮጵያን ሰላምና አንድነት አፍቃሪዎች የሆኑትን ሁሉ በመዝገብ ተይዞ በጅምላ በማንነታቸውና በእምነታቸው እየተለዩ ማረድ፣ በድንጋይ ቀጥቅጦ መግደል፣ በእሳት ማቃጠል፣ ሀብት ንብረታቸው በጠራራ ፀሀይ መዝረፍን የማያስቆም መንግስት አገራችንን ወደእልቂትና ጥፋት እየመራት ነው። ለዚህ ሁሉ ጥፋት መሰረቱ ደግሞ የወያኔ የጥላቻ ፕሮግራም ተሸካሚ የሆነውና በሰፊው ሕዝብ ቅቡልነት ያላገኘው የአፓርታይድ ሕገመንግስት ነው። በኢትዮጵያውያን በሙሉ ተቀባይነት ያለው አዲስ ሕገመንግስት እንዲዘጋጅ የሚሰራና ኢትዮጵያን ወደ እውነተኛ ዲሞክራሲ ያሚያሻግር አመራር አስፈላጊነቱ ግልጽ ነው። ስለዚህ ***የሽግግር መንግስት ተመስርቶ የኢህአዴግ/ብልፅግና አገዛዝ ስልጣኑን ለሽግግር መንግስቱ አስረክቦ ይለቅ ዘንድ ጥሪ እናቀርባለን።***

***ለዚህም ወሳኔ ያነሳሳን ከብዙ በጥቂቱ ለውጥ ተብየው ከመጣ በኋላ፣ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በተለይም በአዲስ አበባ፣ በኦሮምያ፣ በደቡብና በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል በሚባሉት የዘር ማጥፋት ወንጀል በአገዛዙ እውቅናና የዜጋን ሰላም የመጠበቅ ቀዳሚ ኃላፊነትን በትክክል ባለመወጣት ህዝብ፣ በተለይም አማራ ከመቸውም በበለጠ የዘር ማጥፋት ወንጀልና ማፈናቀል ቀን በቀን እየተፈፀመበት ሰቆቃው መፍትሄ በማጣቱ ነው።***

ለዚህም እንደማሳያ፣

- በመዲናችን አዲስ አበባ ከፍተኛ የመሬት ወረራና ብዙ ሺ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ለማይገባቸው ሰዎች በከንቲባው በጎ ፈቃድ የመታደሉ ወንጀል፣ በነገዳቸው ኦሮሞ ያልሆኑትን አዲስ አበቤዎች፣ ከየክፍለ ከተማው ሰዎች ለአመታት ከኖሩበት ቤት ማፈናቀልና ቤታቸውን በላያቸው ላይ አፍርሶ ህዝቡን ቤት አልባ ማድረግ፣

- በኦሮሞ አሸባሪዎች እገታ ውስጥ የሚገኙ የደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ የአማራ ተማሪዎች ከ 10 ወር በላይ ደብዛቸው መጥፋቱና ወላጆቻቸውና ቤተሰቦቻቸው ስለታፈኑት ተማሪዎች ቃለመጠይቅ ስያደርጉ በመንግስት ከፍተኛ ጫና እስከመታሰር እንደደረሰባቸው መታወቁ፣
- በደቡብ ክልል በዚሁ አማራን አሳዶ የማጥፋት ዘመቻ ቤንች ሸኮ ዞን ከሁለት ሳምታት በፊት አማራን ለይቶ በማጥፋት ዘመቻው ብዙዎች መጨፍጨፋቸው፣ ከ5 ሺህ በላይ አማሮች ከቀያቸው እንዲፈናቀሉ በመሆኑ፣ እንዲሁም በዚሁ ጭፍጨፋ ዐማራ በመሆናቸው ብቻ ሙስሊሞች በፀሎት ቦታ ላይ እያሉ በአንድ ቦታ በጅምላ ተጨፍጭፈው ህይወታቸው እንዲያልፍ የተደረገ በመሆኑ፤
- በሰበታ የኦሮሞው ኦርቶዶክስ ካህን፣ የቅዱስ አማኑኤልና ቅዱስ ገብርዔል ቤተክርስቲያን አገልጋይ ቀሲስ ጴጥሮስ ተስፋየ አጋ፣ በተደጋጋሚ የአማራ ሃይማኖት በኦሮሞኛ እንዳያስተምሩ ሲዛትባቸው እንደነበረ ለመንግስት ቢያሳውቁም ገዳዮቹ ምንም እንደማይደረጉ ስለሚያውቁ ቄሱ በዲንጋይ ተወግረው መገደላቸው፣
- አሁንም አሳቃቂ ወንጀል በወለጋ ዞን ጉሊሶ ወረዳ መከላከያ ስፍራውን ለቅቄ እንድወጣ ታዝዣለሁ ብሎ በወጣ በሰዓታት ውስጥ ኦነግ ሸኔ ናቸው የተባሉ ታጣቂዎች አማራውን ስብሰባ ጠርተው በጅምላ መረሸናቸው፤ የአማሮችን መንደር ሙሉ በሙሉ መውደሙ፤ በዚሁ የዘር ፍጅት በወለጋ ዞን ጉሊሶ ወረዳ ውስጥ የሚገኘው ዳዋ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያንን መቃጠሉና ከ30 በላይ ካህናትና ዲያቆናትን መረሸናቸው፤

የአማራ ፍጅት ጭብጥና ኢፍትሀዊ በደል የመፈፀሙ መንስዔ የኢትዮጵያን ህዝብ ጨፍልቆና አጥፍቶ ኦሮሙማን ለመመስረት ለመሆኑ የኦሮሙማው ፕሬዚዳንት “ነፍጠኛውን ሰባብረን” ከማለት ጀምሮ ብዙ ከአንድ መሪ የማይጠበቅ ንግግርን በማድረግ በማናለብኝነት አሳውቀዋል።

የባለጊዜነትና ተረኝነት ስሜት ድፍረት የሰጣቸው፤ ንግግሩ በጠቅላይ ሚንስትር አብይ ተቀባይነት እንዳለውና በስልጣን እንደሚያፀናቸው ያረጋገጡት፤ የኦሮሞው ክልል ፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳ እንዳሉት

*”እኔ ራሱ ቄሮ ነኝ! ብትወዱም ባትወዱም ቄሮን የፈጠረው ኦዴፓ ነው፤ ድል የተገኘውም በስሌት በተሰላ ቁማር ነው! ቁማር በደንብ ነው የተጫውትነው፤ ስለተጫወትንም ነው የበላነው። የቻልነውን አሳምነን ያልቻልነውን ግራ አጋብተን አባይን ተሻግረን ተጫውተናል። አሁን የቤት እመቤት ነን ማለት ነው። ብልፅግናን የሚመራው ኦሮሞ መሆን አለበት፤ ካልሆነ ኦሮሞ የፈቀደለት መሆን አለበት የዚህ አይነት ፓርቲ ነው የመሰረትነው። አማርኛ ቋንቋ እየወረደ ነው ያለው። ኦሮምኛ ቋንቋ የስራ ቋንቋ የመሆኑ ጉዳይ አልቋል። የአዲስ አበባን ዴሞግራፊ በህግም ሆነ በህገወጥ መንገድ እንቀይራለን፣ …….”*

ይህ አሰቃቂ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲፈፀም ይቅርታ ጠይቀው በድጋሚ ስልጣን ላይ የወጡትና ከአንደበታቸው የሚወጣው ቃልና ተግባራቸው የሚፃረረው የቀድሞው ኢህዴግ የአሁኑ ብልፅግና አስቀጣይ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ መንግስት በተደጋጋሚ የአማራውን ሞት አይቶ እንዳለየ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ በመሆን፣ ከታፈኑት ከሚገደሉት ሰዎች ጎን ቆመው አጋርነታቸውን ባለማሳየት የጭፍጨፋው ተባባሪ መሆናቸውን ደጋግመው አሳይተዋል። የአገሪቱ የፀጥታ ተቋም የሆነው መከላከያውና ፓሊሱ የህዝብን ደህንነት ከማስጠበቅ ይልቅ ከገዳዮቹ ጋር በማበር ሲያስገድልና ቤተ እምነት ሲያቃጥል መታየቱ የአደባባይ ሀቅ ሁኗል። አገዛዙ ዛሬም እንደትናንቱ በወለጋ ዞን ጉሊሶ ወረዳ ህዝቡ እባካችሁ አትሂዱብን እያለ የመከላከያ ሰራዊቱን አስነስተው በሰዓታት ልዩነት የአማራ ህዝብ ለስብሰባ ተጠርቶ እንዲጨፈጨፍ አድርገዋል።

አገዛዙ ለኢትዮጵያ ሰላምና አንድነት የሚተጉትን፣ ስለአዲስ አበባ ነዋሪና ስለከተማዋ ሰላም ጥብቅና የቆሙትን የባልዳራስ አመራሮች፤ በከንቲባ ታከለ ኡማ የሚፈፀመውን የከተማዋን ውንብድና በማጋለጣቸው በግፍ በማሰር፤ አማራጭ የመፍትሔ ሀሳብ ያቀረቡትን ፓለቲከኞች እነአቶ ልደቱ አያሌውን ቄሮን አስተብብረዋል ብሎ በውሸት ክስ ማሰር፣ አቶ ልደቱ የልብ ህመም እንዳለባቸውህና ህክምና እንደሚያስፈልጋቸው እየታወቀ ሰብዓዊ የሆነ የህክምና መብታቸውን መከልከል፣ አድልዎውን በግፍ አሳይቷል።

ለዚህ ሁሉ ወንጀልና ጥቃት  አንደኛ ተባባሪው የሆነው በወያኔ  ተጠፍጥፎ የተሰራው ብአዴን/ አዴፓ በሉሌነቱ ቀጥሎ በህግ መጠየቅ ለሚገባቸው የኦዴፓ ባለስልጣናት **“ደግ አደረጋችሁ፤ ያላችሁትንም የምትሰሩትንም እንደግፋለን፤ ከጎናችሁ ነን፤”** ብሎ ነሸመልስ አብዲሳን ካባ በማልበስ በሕዝብ ስቃይና እምባ መሳለቁ ሳያንስ አማራ ተጨፈጨፈ ብሎ አብን የጠራው ሰላማዊ ሰልፍ አስፈራርቶ በመከልከል ከአማራው ገዳዮች ጋር እጅና ጓንት ሆነው እንደሚሰሩ አስመስክሯል።

በህዝብ ግፊት ተነቃንቆ ተገፍትሮ ሊወድቅ ቋፍ ላይ የነበረው ኢህአዴግ መልሶ ይቅር በሉኝ ብሎ ስልጣን የጨበጠው ከወያኔ ወደኦሮሙማ የበላይነት መሻገሩ፣ የህዝብን ማንነት ጨፍልቆ በመጠፋፋት ላይ የተመሰረተ የጥፋት አገዛዝ ለማስቀጠል ቆርጦ በመነሳቱና ለኢትዮጵያ ህዝብ ንቀቱን በተደጋጋሚ ማሳያቱ በጣም ቢያሳዝንም መፍትሄው የኢህአዴግ/ብልፅግና አገዛዝ ስልጣኑን ለኢትዮጵያ ህዝብ አስረክቦ መልቀቁ ብቻ ነው።

ስለዚህ፣

- የኢህአዴግ/ብልፅግና በንፁሃን ደም፣ በተለይም በአማራ ደም ስልጣን ጨብጦ መቀጠል ስለሌለበት በአስቸኳይ ሁሉን አካታች የሽግግር መንግስት ተመስርቶ  ስልጣኑን ለህዝብ እንዲያስረክብ፣
- የኢህአዴግዊ የዘር ፓለቲካ ህገመንግስቱ፣ በጎጥ አሳቤ ያለው አምባገነን ጎጠኛ መሪዎችን አያበለፅገ፣  አብሮ ተዋህዶ፣ ተጋብቶና ተጣምሮ የሆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ በጎጥ በመለያየት የንፁሃን ደም የሚያፈስና ኢትዮጵያዊነትን ከስሩ የሚንድ ስለሆነ  በኢትዮጵያዊ ህገመንግስት እንዲቀየር፣
- የጥቃት ኢላማ የሆነው የአማራ ህዝብም የህግ የበላይነት የሚያስከብርና ጥቃት ከሚፈፀምበት ሰላማዊ ህዝብ ጎን የሚቆም መንግስት ስለሌለ፣ እራስን ከሞት መከላከል ደግሞ ተፈጥሯዊ ግዴታ ስለሆነ እርስ በእርስ እየተናበበ ራሱን፣ ቤተሰቡንና አካባቢውን ሁሉ ከጥቃት እንዲጠብቅ፣
- የአማራ ህዝብ የሚፈጀው በታለመና  በታቀደ የዘር ጭፍጨፋ እንጅ በግጭት ስላልሆነ፣ በስሙ “የዘር ጭፍጨፋ” የሚል እውቅና እንዲሰጠውና በየአካባቢው ለፈሰሰው ደምና ማፈናቀል በአስቸኳይ ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን ተቋቁሞ እንዲያጣራ፣
- የኢህአዴግ አፓርታይድ አገዛዝ በ1983 ዓ/ም የመንግስት ሥልጣንን ከተቆጣጠረ ጅምሮ የአገዛዙ ቱባ አመራሮች በፈጽሟቸው ጭካኔ የተሞላባቸው ኢሰባዊ ተጋባሮቻቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያላቸውን ጠላትነትና ንቀት ደጋግመው አስመስክረዋል። ሰሞኑን የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አቀንቃኙ ወያኔ / ኢህአዴግና የመደመር / ኦሮሚማ አራማጇው ብልጽግና / ኢህአዴግ በሚያደርጉት መንግስትን የመቆጣጠር ጦርነት የኢትዮጵያን ህዝብ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍልና ኢትዮጵያንም የውስጥና የውጭ ሰላሟን ወደ ተባባሰ ችግር ወስጥ የሚያስገባ በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም ዐማራው ይህ የሱ ጦርነት አለመሆኑን ተገንዝቦ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግና በአንጻሩ ዘላቂ ጥቅሙንና ሰላሙን እውን ለማድረግ እንዚህን ሁለት እኩይ ሀይሎችን የጫኑበትን የጥፋት ቀንበር ከጫንቃው ላይ ለማስወገድ በጎበዝ አለቆች እየተመራ ትግሉን እንዲያፋፍም፣

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት በሃምሌ ወር 2012 ”በዋናነት በዐማራ ህዝብ ላይ ባነጣጠረውና የጉራጌ ነገድ ተወላጆችን ብሎም ኦሮሞ ባልሆኑት ኢትዮጵያውያን ላይ የተፈፀመውን የዘር ምንጠራና ጭፍጨፋ በጥብቅ እናወግዛለን። ” በሚል ርዕስ ባወጣው መግለጫ በድምፃዊ ሀጫሉ ሰበብ በፅንፈኛ ኦሮሞ ቄሮ በአሰቃቂ ሁኔታ ለተገደሉት ኢትዮጵያውያን የሰማዕታት ሀውልት በዋና ከተማችን እንዲቆምላቸው ባቀረበው ጥሪ መሰረት አሁንም በድጋሚ በዚህ አገዛዝ በግፍ ለተጨፈጨፉት ለአማራ፣ ጉራጌ፣ ጋሞ፣ ወላይታና ሌሎችም ወገኖቻችን የዘር ጭፍጨፋ መሆኑ እውቅና ተሰጥቶት በግፍ ደማቸው ለፈሰሰው ሁሉ የሰማዕታት ሀውልት እንዲሰራላቸው ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ይጠይቃል።

አንድ ዐማራ ለሁሉም ዐማራ፤ ሁሉም ዐማራ ለዐንድ ዐማራ!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!